Ethiopiawinet Radio

Ethiopiawinet.net



ይድረስ ለአቶ መለሰ ልጆች

ነቢዩ ዓለማየሁ እባላለሁ። የእናንተ እኩያ ነኝ። እኔ ግን በሕይወት ልኖር የቻልኩት ለ14 ዓመታት "ብቻ" ሲሆን፤ ግንቦት 30/1997 እኩለ ቀን በ/ትቤት ደጃፍ ላይ ከነዩኒፎርሜና ደብተሮቼ በእናንተ አባት ትዕዛዝ ባልታወቀ ክፉ ወታደር ተኩስ ነፍሴ ከስጋዬ ተለይታለች።

ገላዬን በጥይት ቢያፈርሱትም ነፍሴ ግን የሕጻናት አባት የሆነው ጌታ ኢየሱስ እቅፍ ውስጥ በመላእክት አቀራቢ. ገብታለች። ሃሌ ሉያ ! ይህንን መልእክት ዜጎች እንዲገደሉ ላዘዙት አባታችሁ በእናንተ በኩል አስተላልፍ ዘንድ ፍቃዱ የጌታ ሆኖአል። ስማችሁን ለማወቅ ባለመቻሌ በሃገራችን በቤት ስምነት በተለመዱት አቡሽና ሚሚ እያልኩ ስሜቴን ልግለጽላችሁ።

አቡ! ለአክሱም ሃውልት በዓል ጊዜ እናቴ እናንተን በቲቪ አይታ እንድመለከታችሁ ስታደርገኝ እኩያዎቼ ስለሆናችሁ ትልቅ ስንሆን ተገናኝተን ስለምን ልናወራ እንደምንችል አሰላስል ነበር።

አቡሼ መለስና ሚሚ መለስ፤

እናታችሁ እማማ አዜብ ያማጡትን ያህል የእኔም እናት ውብዬ አምጣለች። እናንተ ስትወለዱ የተፈጠረው የወላጆቻችሁ ደስታ እኔም ቤተሰብ ዘንድ አለ። ማሚዬ! አዜብ ከጥናት በሁዋላ አልጋችሁ ላይ ጸጉራችሁን አሻሽተው ግንባሮቻችሁን ስመው በእያንዳንዱ ሌሊት እየደባበሱ እንደሚያስታኙዋችሁ ሁሉ የእኔም ማሚዬ ውብ ዓለም እስከ ግንቦት 30/1997 ሌሊት ድረስ በወላጅ አይኑዋ እያየችኝ የመጨረሻ መሆኑን ሳትገምት ደባብሳ አስተኝታኛለች።

አቡሼና መለስ ዜናዊ!

ወላጆቻችሁ፤ አድጋችሁ ለቁም ነገር በቅታችሁ ለወግ ማዕረግ እንድትደርሱ ያላቸውን መልካም ምኞት ሁሉ እናቴም ለእኔ ለልጇዋ እንደሚኖሩዋት ታውቃላችሁ። ይህ ምኞት ግን ባጭሩ ተገታ። የማዝነው የእናቴ ምኞት የተገታው በእኔ ጥረትና ትጋት ሳይሆን፣ በጌታ ዘንድ ትልቅ ሐጢአት በሆነው በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተገድዬ ነው።

ይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ " ሃገራችን" እያልን ባንዲራዋ ሥር ቆመን የምንዘምርላት ሃገር መሪ በሆኑት "አባታችሁ" ቀጭን ትዕዛዝ ተገድዬ ሕልሜ መምከኑ ነው። አቡሽ! አባታችሁ ያስገደሉኝ ለዲሞክራሲ ሲሉ ነው ይባላል ግን እኮ ! ዲሞክራሲ ሰው እንደማይገድል፤ በዲሞክራሲ ክፉ መሪ እንደሌለ የሲቪክ መምህራን አስተምረውናል። እናንተስ አልተማራችሁም?

እናንተና እኔ እንኩዋን ባንክ ልንዘርፍ፣ ባንክ ቤት ገብተን እንደማናውቅ አምናለሁ። አሁን ድረስ አስፋልት ላይ ስንጫወት ወይ ስናጠፋ ታላቆቻችን " ዋ ! ፓሊስ እንጠራልን ትታሰራላችሁ"እያሉን ነው ያደግነው። መቼም በዚች አቅም አቡሼ " ... ከፓለስ መሣሪያ ነጥቆ እስረኛ ለማስፈታት ሞከረ " ቢባል አባትህ እንደማይቀበሉ ተስፋ አደርጋለሁ። በኔ ላይ ግን ሆነ።

እነ አቡ!

አባታችሁ ግን ለምን ገደሉኝ!

እናቴ መኝታዬ ሥር ተንበርክካ ፎቶዬን ደረቱዋ ላይ ለጥፋ ሰውነቱዋ በእንባዋ በእየለቱ ሲርስ ቢያዩ አባትና እናትህ ምን ይሉ ይሆን? "ቁም!" ብሎ የገደለኝ አረመኔው ወታደር "እናቴ ጋ ቤት ልሄድ ነው" እያልኩት አስፋልት ላይ ከጣለኝ በሁዋላ ትልቅ ጥይት የሕፃን ደረቴ ላይ ሲለቅ ምን ተሰማው? ዛሬ ልጅ ባይኖረው ነገ ይኖረውል። ፍርዱን አይንሳው!! ይህ ጨካኝ፤ የሚያልፈው የሚጠፋው የአባታችሁ የአቶ መለስ መንግስት ወታደር ሲሆን፣ እኔ ግን የዘልዓለሙ የማያልፈው የኢየሱስ መንግስት ብላቴና ወታደር ሆኛለሁ። ሃሌ ሉያ!

ሚሚዬ!

ከጥቂት ዓመታት በፊት በነበረው የባድመ ጦርነት ጊዜ ሲነገር እንደሰማሁት፣ ወታደር ማለት እኛ በሰላም እንድንኖር ሲል እርሱ የሚሞትልን መሆኑን ነበር።

ታዳጊ

ወጣት ነቢዩ ዓለማየሁ

(የእምነቴ ፈተና በደበበ እሸቱ የተገኘ)

(መለስ ሼራተን ከልጁ ጋር በግድያው ምሽት)

## June 8: Bloody Wednesday for Addis Residents & Partyting at Sheraton for Meles and Officials